# በኢፌዴሪ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

## ስደተኞች በስራ የሚሰማሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 08/2012

# መግቢያ

አገራችን ለዘመናት ስደተኞችን ተቀብላ በማስተናገድ ቀደምት ታሪክ ያላት አገር ስትሆን በአሁኑ ወቅትም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች አስጠልላ ትገኛለች፡፡

መንግስት የስደተኞችን ጉዳይ አለማቀፋዊ ባህሪ ያለው መሆኑን በመረዳት በአለማችን እየሰፋ ያለውን የተፈናቀዮች እና ስደተኞች ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ስደተኞች ለአንድ ሀገር ሸክም ሳይሆኑ እንደ ሀብት በመቁጠርም የልማት አጋር እንዲሆኑ ለማስቻል እና በስደተኛ መጠለያ ጣቢያ አካባቢዎችም ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል መንግስት ከዚህ በፊት በስራ ላይ የነበረውን የስደተኛ ህግ በማሻሻል አዋጅ ቁጥር 1110/2011 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

አዋጁም ስደተኞችን ወደ ስራ ለማስገባት የተለያዩ የሀገሪቷ ህጎችን ያጣጠመ እንዲሆን ከመደረጉም ባሻገር ስደተኞች መንግስት ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር የጋራ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ወደ ስራ የሚሰማሩበት እንዲሁም ለውጭ ሀገር ዜጎች የተፈቀዱ የስራ ዘርፎች ላይ ስደተኛው የስራ ፈቃድ በማውጣት መስራት ስለሚቻልበት ሁኔታ ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም ይህ አዋጅ በሀገሪቷ ያልነበረውን አዲስ የስደተኞች አያያዝ በተሻለ ሁኔታ ያስቀመጠና በዚህ ህግ ውስጥ ህጉን ለመፈፀም ስደተኞች ከወጭ ሀገር ዜጎች በተሻላ የሚስተናገዱበትን አሰራር የዘረጋ ቢሆንም አዋጁ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ስደተኛው በግል፣ በቅጥር እንዲሁም በጋራ ሊሰማሩባቸው በሚችሉ ስራዎች ላይ ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓትና የህግ ማዕቀፍ ባለማስቀመጡ ምክንያት አዋጁን ለማስፈጸም ወሳኝ የሆኑ የአጋር አካትን በማሳተፍ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. የመመሪያው አስፈላጊነት

የስደተኞች፣ ጥገኝነት ጠያቂዎችና የአካባቢ ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እንዲሁም የጋራ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የስደተኞች አዋጅ ጉዳይ አንቀጽ 26 የስደተኞችን የመሥራት መብት የደነገገ በመሆኑ ይህንን ድንጋጌ በአግባቡ ለመተግበር ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

### 2. የአውጭው ባለሥልጣን

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 46 (2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የስደተኞችን የስራ መብት ሁኔታዎችን ለማስፈጸም ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 3. አጭር ርዕስ

ለኤፌዲሪ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ስደተኞች በሥራ ላይ የሚሠማሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 08/2012 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 4. ትርጉም

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ"** ማለት አዋጅ ቁጥር 1110/2011 ማለት ነው፡፡
2. **"ሚኒስቴር"** ማለት የኢፌዲሪ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማለት ነው፡፡
3. **"ኤጀንሲ"** ማለት የኢፌዲሪ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡
4. **"ስደተኛ"፣ "ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ"፣ "ጥገኝነት ጠያቂ"፣እና "ቤተሰብ"** ማለት በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ያለው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

5. **"የጋራ ፕሮጀክት"** ማለት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ እና በኢትዮጵያ መንግስት ስምምነት መሰረት ዕዉቅና ያገኙ ስደተኞች እና ኢትዮጵያዉያን በጋራ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚሆኑበት የከተማ ወይም የገጠር ልማት ፕሮጄክት ነዉ፡፡

6. **"የመኖሪያ ፈቃድ"** ማለት አንድ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በአንድ ተለይቶ በተቀመጠ የጋራ ፕሮጀክት ውስጥ ከኢትዮጵያዉያን ዜጎች ጋር ተመሳሳይ አያያዝ በማግኘት ለመስራት እንዲችል በኤጀንሲው የሚሰጠውና እንደየአስፈላጊነቱ በአምስት አመት የሚታደስ ፈቃድ ነው፡፡

7. **"የቅጥር ሥራ"** ማለት ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በሙያዉ ወይም በጉልበቱ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ በክፍያ የሚሠራ ማለት ነው፡፡

8. **"የግል ስራ"** ማለት በተናጥልም ይሁን በጋራ አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ከሚመለከታቸው ፈቃድ ሰጪ የመንግስት አካላት ፈቃድ በማውጣት እንደ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛና ጥቃቅን፣ እደጥበባትና ንግድ በመሳሰሉ ዘርፎች በመሰማራት ዕውቅና ባገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚሰራ ስራ ነው፡፡

9. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

10. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## 5. መርሆዎች

ዕውቅና ካገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች የስራ መብት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የሚሰጡ አገልግሎቶች፤

1. ቀልጣፋ፣ ወጥ፣ ግልፅና ፍትሃዊ እንዲሁም ጥራታቸውን የጠበቁ፣ ተደራሽና በዘመናዊ መልኩ የተደራጁ እንዲሆኑ ማድረግ፣

2. በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ላይ የስደተኞች ጥበቃና ከለላን አስመልክቶ ከተቀመጡ መርሆዎች ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፤

## 6. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ዕውቅና ባገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ በቀጣሪ ድርጅቶችና፣ በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ተሳትፎ በሚኖራቸው ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## በጋራ ኘሮጀክት ስለመሠማራት

## 7. በጋራ ኘሮጀክት ለመሠማራት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ በኤጀንሲውና በኘሮጀክቱ የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት በጋራ ኘሮጀክቱ እንዲሣተፍ ከተመረጠ የሥራ ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልገው ከኤጀንሲው የመኖሪያ ፈቃድ በማግኘት በጋራ ኘሮጀክት ላይ ለመሥራት ይችላል፡፡

2. ከኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ የፈጸመ ወይም አንድና ከአንድ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት ያላቸው ልጆች ያለው ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ይህንን የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ ከኤጀንሲው ከተሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተጠቀሰው የጋራ ፕሮጀክት ለመሳተፍ የመኖሪያ ፍቃድ ማውጣት አያስፈልገውም፡፡

## 8. የመኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎች

ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ የመኖሪያ ፈቃድ ማውጣት የሚችለው፤

1. በአንድ የጋራ ፕሮጀክት በመታቀፍ ለመስራት የፕሮጀክቱን መስፈርት ሲያሟላ እና ኤጀንሲው በሚያወጣው አሰራር መሰረት ሲመረጥ፣
2. ስደተኛው ከፀጥታና ወንጀል ጋር በተያያዘ በመጣራት ወይም በክስ ሂደት ላይ አለመሆኑን ኤጀንሲው ሲያረጋግጥ፣
3. የስደተኝነት ዕውቅና ከተሰጠው በኋላ 3(ሶስት) ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ በስደተኝነት የቆየ ከሆነ ነው፡፡

## 9. የመኖሪያ ፍቃድ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች

1. የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጠው ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ያለ መንቀሳቀሻ ፈቃድ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር እንዲሁም የመኖሪያ ፈቃዱን ባገኘበት የጋራ ፕሮጀክት ውስጥ የመስራት መብት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የመኖሪያ ፈቃዱን ያገኘው በጋራ ፕሮጀክት ለመስራት የተመረጠ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ የቤተሰብ አባል በመሆን ከሆነ በዚሁ የመኖሪያ ፈቃድ በመጠቀም የመስራት መብት የለውም፡፡

## 10. የመኖሪያ ፍቃድ የተሰጣቸው ስደተኞች ግዴታዎች

ማንኛውም የመኖሪያ ፍቃድ የተሰጠው ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ፤

1. መኖሪያ ፈቃዱን ፍቃዱ ለተሰጠበት የጋራ ፕሮጀክት ብቻ መጠቀም አለበት፡፡

2. በሕገወጥ ስራዎችና ለሕዝብ ሞራል ተጻራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ ያለመሠማራትና የአገሪቱን ሕጎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## 11. የመኖሪያ ፍቃድ አቀራረብና መስፈርቶች

1. በጋራ ፕሮጀክት ለመሳተፍ በኤጀንሲው የተመረጠ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ አባላት አዲስ የመኖሪያ ፍቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው በራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ ብቻ ነው፡፡

2. ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ አዲስ የመኖሪያ ፍቃድ ለማውጣት የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. በቅጽ የተሞላ የመኖሪያ ፍቃድ ማመልከቻ፣

ለ. ስደተኝነቱን የሚገልጽ በኤጀንሲው የተሰጠው የታደሰ መታወቂያ፣

ሐ. የፓስፖርት መጠን ያላቸው የስደተኛው አራት ጉርድፎቶግራፎች፣

መ.የመኖሪያ ፍቃዱ የጠየቀው ለባል/ሚስት ከሆነ የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣

ሠ. የመኖሪያ ፍቃዱ የተጠየቀው ለአካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ ከሆነ የልደት የምስክር ወረቀት፣

ረ. ለሌሎች የቤተሰብ አባላት ኤጀንሲው የሰጠው ማረጋገጫ፣

ሰ. እንዳግባብነቱ የሥራ ቅጥር ውል ወይም የፀና የንግድ ፈቃድ ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር አባልነት ማስረጃ

## 12. የመኖርያ ፍቃድ እድሳት አቀራረብና መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ የመኖሪያ ፍቃዱ ወይም የቤተሰቡ የመኖሪያ ፍቃድ የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት ባለው (2) ሁለት ወር ውስጥ የሚከተሉትን በማሟላት በአካል ቀርቦ ለኤጀንሲው ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. የመኖሪያ ፍቃድ የእድሳት ማመልከቻ፣
ለ. ስደተኝነትን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ፣
ሐ. የመኖሪያ ፈቃድ፣
መ. የሥራ ቅጥር ውል ወይም የፀና የንግድ ፈቃድ ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር አባልነት ማስረጃ

ሠ. የፓስፖርት መጠን ያላቸው ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳዉ የስደተኛው አራት ጉርድ ፎቶግራፎች፣

## 13. የመኖሪያ ፈቃድ ስለመተካት

1. የጠፋን ወይም የተበላሸን የመኖሪያ ፍቃድ ለመተካት ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው በጋራ ፕሮጄክት ለመስራት የመኖሪያ ፍቃዱን ባገኘው ስደተኛ አማካኝነት ብቻ ነው፡፡

2. አንድ ስደተኛ የጠፋ ወይም የተበላሸ የመኖሪያ ፈቃድ ምትክ ለማግኘት ሲጠይቅ፤

   ሀ. የጽሁፍ ማመልከቻ፤

   ለ. የመኖሪያ ፍቃዱ ከጠፋ ለመጥፋቱ የሚያረጋግጥ ስልጣን ከተሰጠው የፖሊስ ተቋም የተሰጠ ደብዳቤ ወይም ለኤጀንሲው ያመለከተ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፤

   ሐ. የመኖሪያ ፍቃዱ ከተበላሸ የተበላሸውን ቀሪ ማስረጃ፤

   መ. ስደተኝነትን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ፤

   ሠ. የፓስፖርት መጠን ያላቸው የስደተኛው ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳዉ አራት ጉርድ ፎቶግራፎች፤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3.የጠፋው የመኖሪያ ፍቃድ ቁጥሩ ተጠቅሶ መታገድ አለበት የተበላሸ ከሆነ ደግሞ የተበላሸዉን አምጥቶ ለኤጀንሲው ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.የመኖሪያ ፍቃድ ምትክ የተሰጠው ስደተኛ የጠፋውን ካገኘው ወይም የሚገኝበትን ካወቀ ወድያውኑ ለኤጀንሲው መመለስ ወይም ያለበትን ማሳወቅ አለበት፡፡

## 14. የመኖሪያ ፍቃድ የሚሰረዝበት ሁኔታዎች

የመኖሪያ ፍቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ይሠረዛል፤

1. የመኖሪያ ፍቃዱ የተሰጠው ስደተኛ በራሱ ፈቃድ ሲመልስ፤
2. ስደተኛው የተሰማራበት ስራ ከተቋረጠ፤
3. ስደተኛው የመኖሪያ ፍቃድ በተሰጠው ስራ ላይ ያለ በቂ ምክንያት ለሶስት ወራት አለመገኘቱ ከተረጋገጠ፤
4. ስደተኛው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን መተላለፉ ከተረጋገጠ፤

5. የስደተኝነት ዕውቅናውን ያጣ ከሆነ፤

6. ስደተኛው ከአገር መውጣቱ ከተረጋገጠ፤

7. የመኖሪያ ፍቃዱ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በማታለል፣ በማጭበርበር፣ ወይም በሌላ ሕገ ወጥ መንገድ የተሰጠው መሆኑ ከተረጋገጠ፤

8. የመኖሪያ ፍቃዱ ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካለ በቂ ምክንያት ሳያሳድስ ከቀረ፤

9. ስደተኛው ፍቃዱን ይዞ መቆየቱ ለሀገር ጥቅምና ደህንነት ተገቢ አለመሆኑ በኤጀንሲው ሲታመን።

## 15. በመኖሪያ ፈቃድ የሚፈጠር ቅሬታ በተመለከተ ስለሚቀርብ አቤቱታ፡-

በመኖሪያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ስረዛ እና እድሣት ላይ ለሚከሰቱ ማናቸውም ቅሬታዎች ደረጃውን ጠብቆ ዘርፉን እስከሚመራው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ድረስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ያልረካ ወደ ዋና ዳይሬክተሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።ይህ የመጨረሻ ይሆናል።

# ክፍል ሦስት

# በቅጥር ሥራ ስለመሠማራት

## 16. በቅጥር ሥራ ለመሠማራት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች

1. እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የስራ ፈቃድ በማውጣት ወደ ስራ ሊሰማራ ይችላል።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ የተቀመጠው ቢኖርም በጋራ ፕሮጀክት ላይ ለመስራት የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጠው ስደተኛ የስራ ፈቃድ ሳያስፈልገው የመኖሪያ ፈቃድ በተሰጠበት ፕሮጀክት ውስጥ ተቀጥሮ መስራት ይችላል።

3. በስደተኞች አዋጅ አንቀፅ 26 (10) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢትዮጵያዊ ዜጋ ጋር ህጋዊ ጋብቻ የፈፀመ ወይም አንድና ከአንድ በላይ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ልጆች ያለው ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የስራ ፈቃድ ሳያስፈልገው ተቀጥሮ መስራት ይችላል።

4. አንድ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ተቀጥሮ መስራት የሚችለው መብቱን ያገኘው፡-

ሀ/ በጋብቻ ከሆነ የጋብቻውን ትክክለኛነትና የጋብቻ ምስክር ወረቀቱ መመዝገብ በኤጀንሲው ሲረጋገጥ ወይም

ለ/ በልጅ ከሆነ የልጁ የኢትዮጵያዊ ዜግነት ማስረጃ ሲቀርብ ወይም፣

ሐ/ ኤጀንሲው በሚያወጣው አሰራር ስደተኛው ያለስራ ፈቃድ መስራት እንደሚችል የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ ሲሰጠው ነው፡፡

## 17. በአሰሪ ስለሚቀርብ የቅጥር ጥያቄ

1. በኢትዮጵያውያን ሊሸፈን በማይችል የስራ መስክ ላይ ስደተኛውን ወይም ጥገኝነት ጠያቂን ቀጥሮ ለማሰራት የሚፈልግ አሰሪ የኤጀንሲውን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ከሚኒስቴሩ ህጋዊ ውክልና ከተሰጠው አካል የስራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤

2. በዚህ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተው የስራ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው አሰሪው ስደተኛውን ወይም ጥገኝነት ጠያቂውን በድርጅቱ ውስጥ ለመቅጠር ብቻ እና ፈቃድ በተጠየቀበት የስራ መደብ ላይ ለመስራት ብቻ ነው፤

## 18. ስለ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ

1. እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ከጋራ ኘሮጀክት ውጪ በቅጥር ሥራ ለመሠማራት የሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ከኤጀንሲው ፈቃድ የተጠየቀበት ስራ በኢትዮጵያውያን ሊሸፈን የማይችል መሆኑን አግባብነት ካለው ሴክተር መስሪያ ቤት በማረጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤ ለሚኒስቴሩ ይፅፋል፣

2. ከላይ በአንቀጽ 17 መሠረት ስደተኛን ወይም ጥገኝነት ጠያቂን ቀጥሮ ለማሰራት አሠሪው ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ ኤጀንሲው አስፈላጊውን ማጣራት በማካሄድ ለሚኒስቴሩ የድጋፍ ደብዳቤ ይፅፋል፤

3. ማንኛውም አሠሪ ለሚቀጥረው ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ አዲስ የሥራ ፈቃድ ሲያወጣ ወይም ሲያድስ፡-

   ሀ. በፓስፖርት ምትክ ከኤጀንሲው ለስደተኛው ወይም ጥገኝነት ጠያቂው የተሰጠውን የታደሰ መታወቂያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

   ለ. ዕውቅና ያገኘው ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂው ማንኛውም ዓይነት ቪዛ ወይም መኖሪያ ፈቃድ እንዲያቀርብ አይጠየቅም፣

   ሐ. በኤጀንሲው የሚሰጥ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፣

4. አሠሪው ቀጥሮ የሚያሰራውን ስደተኛ ወይም ዕውቅና የተሰጠውን ጥገኝነት ጠያቂ በተመለከተ በማንኛውም ጉዳይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያቀርብ ለኤጀንሲው ተመሣሣይ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## በግል ስራ ስለመሰማራት

### 19. በግል ስራ ለመሰማራት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በአገሪቱ ህጎች መሰረት አግባብነት ካላቸው የመንግስት ፈቃድ ሰጪ አካላት ፈቃድ በማውጣት የውጪ ሀገር ዜጎች ሊሰማሩባቸው በሚችሉባቸው የስራ መስኮች ላይ በተናጠል ወይም በቡድን በግል ስራ ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ በተደነገገው መሰረት ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ የመኖሪያ ፈቃድ በማውጣት በግል ስራ ለመሰማራት የሚችለው፡-

   ሀ/ ኤጀንሲው ባፀደቀውና ወደ ተግባር በገባው የጋራ ፕሮጀክት ለመሳተፍ ሲሆን፣

   ለ/ ከኢሚግሬሽን፣ የዜግነት ጉዳይና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የመኖሪያ ፈቃድ በማውጣት፤

   ሐ/ ስደተኛው ወይም ጥገኝነት ጠያቂው በግል ወይም በቡድን ስራ ላይ ለመሰማራት ለኤጀንሲው ጥያቄ ሲያቀርብ፣

   መ/ ኤጀንሲው ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል የድጋፍ ደብዳቤ ሲፅፍ እና፣

   ሠ/ የሚመለከተው የመንግስት ፈቃድ ሰጪ አካል ለስደተኛውና ለጥገኝነት ጠያቂው ተገቢውን ፈቃድ ሲሰጥ፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሁለት የተደነገገው ቢኖርም

   ሀ/ በኤጀንሲው የመኖሪያ ፈቃድ ያገኘ ስደተኛ የስራ ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልገው በጋራ ፕሮጀክቶች ውስጥ በግል ስራ ሊሰማራ ይችላል፤

   ለ/ በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 26(9) በተደነገገው መሰረት ከኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ህጋዊ ጋብቻ ወይም ከአንድ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት ያላቸው ልጆች ያለው ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የመኖሪያ ፈቃድ ሳያስፈልገው አግባብነት ካለው የመንግስት ፈቃድ ሰጪ አካል ፈቃድ በማውጣት የጋራ ፕሮጀክት ወይም ለኢትዮጵያውያን በተገደቡ የስራ መስኮች ውስጥ በግል ስራ ሊሰማራ ይችላል፤

ሐ/ አንድ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረት ፈቃድ አውጥቶ በግል መስራት የሚችለው መብቱን ያገኘው በጋብቻ ከሆነ የጋብቻውን ትክክለኛነትና የጋብቻ የምስክር ወረቀቱ መመዝገቡ በኤጀንሲው ሲረጋገጥ፤ ወይም በልጅ ከሆነ የልጁ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ማስረጃ ሲያቀርብ ኤጀንሲው በሚያወጣው አሰራር መሰረት ያለመኖሪያ ፈቃድ መስራት እንደሚችል የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ ሲሰጠው ነው፡፡

4. በእርሻና መስኖ ስራዎች ላይ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎችና ኢትዮጵያውያን በጋራ ፕሮጀክት መሳተፍ የሚችሉት ፕሮጀክቱ በሚተገበርበት ክልል መንግስትና በኤጀንሲው መካከል ስምምነት በተደረሰባቸው የሊዝ ማዕቀፎች መሰረት ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**20.** በዚህ መመሪያ መሰረት የስደተኞችና ጥገኝ ነት ጠያቂዎች በስራ የመሰማራት ጥያቄ ሲስተናገድ ኤጀንሲዉ ለአካል ጉዳተኞ፤ ሴቶች፤አረጋዊያን እና ሌሎች ድጋፍ ለሚሹ አካላት አስፈላጊዉን ልዩ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ ይህንንም ይህን መመሪያ ተከትሎ ኤጀንሲዉ በሚያዘጋጀዉ የአፈፃፀም መስፈርት ማኑዋል ዉስጥ በዝርዝር ማካተትና መተግበር አለበት፡፡

### 21. ምስጢር ስለመጠበቅ

ማንኛውም አሠሪ ወይም ይህንን መመሪያ የሚያስፈጽም ማንኛውም አካል በስደተኛው ወይም ጥገኝነት ጠያቂው የቅጥር ሥራ አማካኝነት ያገኘውን ማንኛውም መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታና ያለኤጀንሲው እውቅና ለሌሎች አካላት ለስደተኛው ወይም ጥገኝነት ጠያቂው መረጃ አይሰበስብም ወይም አሳልፎ አይሰጥም፡፡

### 22. ክትትልና ቁጥጥር

በስራ ላይ የሚሳተፉ ስደተኞችን በተመለከተ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መተግበራቸውን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

### 23. ስለአገልግሎት ክፍያ

የመኖሪያ ፍቃድና የስራ ፍቃድ ለማውጣት ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች የአገልግሎት ክፍያ አይከፍሉም፡፡

### 24. የአስፈፃሚ አካላት ሚና

1. ኤጀንሲው ለስደተኞች የሰጠውን የመኖሪያ ፈቃድ በተመለከተ ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ እንደ አስፈላጊነቱ መረጃ ይሰጣል፡፡

2. ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ መሰረት በስራ ለመሰማራት ለሚጠይቁ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች አስፈላጊውን የስደተኝነት ምዝገባ ማረጋገጫ እና የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከታቸዉ አካላት ይጽፍላቸዋል፡፡

3. ሚኒስቴሩ ወይም ሕጋዊ ውክልና የተሰጠው አካል ለእያንዳንዱ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የስራ ፈቃድ ሲሰጥ ለኤጀንሲው ያሳውቃል፡፡

4. እንደአስፈላጊነቱ ኤጀንሲው የስደተኞችና ጥገኝት ጠያቂዎችን የስራ መብት ሁኔታዎች አፈጻጸም በተመለከተ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነርና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በትብበር ይሰራል፡፡

## 25. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 20/2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሣሥ 20/2012 ዓ.ም

ከበደ ጫኔ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ
ዋና ዳይሬክተር